**ኤፐሪል 30፣ QuickNotes**

**Madeline Hanington የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የዓመቱ መምህርት "MCPS Teacher of the Year" በመሆን ተሰይማለች።**

የ Hallie Wells ሚድል ስኩል መምህርት **Madeline Hanington** የ 2019–2020 የ MCPS የዓመቱ መምህርት በመሆን የተሰየመችው በ17ኛው ዓመታዊ ለልጆች እውቀት ያስጨበጡ ሻምፒዮኖች በትምህርት የላቀ እውቅና የመስጠት የሽልማት ዝግጅት/አውድ ላይ ነው።

Hanington የእንግሊዝኛ ይዘት ባለሙያ/English content specialist እና በሀሊ ወልስ ት/ቤት/Hallie Wells መምህርት ናት። ከ 2016 ጀምሮ የትምህርት ቤቱ ባልደረባ ናት።

Hanington ከዚህ በኋላ ለሜሪላንድ የዓመቱ መምህርነት ውድድር ትቀጥላለች። በአንድ ወቅት እርሷ ራሷ የእንግሊዝኛ ተማሪ የነበረች እና በአርት የመጀመሪያ ዲግሪ ያዘች ስትሆን የትምህርት አቀራረቧ ቀስቃሽ፣ ተፈታታኝ፣ ፈጠራን የሚጠይቅ እና እውቀትን የሚያዳብር አይነት አቀራረብ ነው። አቀራረቧ ውጤታማ መሆኑን መረጃዎች ያረጋግጣሉ። እርሷ የፈጠረቻቸው እና ተግባራዊ ያደረገቻቸው አካደሚያዊ ጣልቃ ፕሮግራሞች በሜሪላንድ የምዘና ነጥቦችን ቢያንስ በአምስት ፐርሰንት ከፍ አድርጓል። የ 2011 Milken Educator ሽልማት አሸናፊ የሆነችው Hanington ለምህርት ቤቱ የእንግሊዝኛ አስተማሪዎች ሜንቶር ብቻ ሳትሆን፣ ሌሎች ባልደረቦችን እና ከ Hallie Wells ት/ቤት ውጪ ያሉትንም በማማከር ትረዳቸዋለች። በ "Junior National Honor Society"፣ በ "school's Lady Scholars program" እና ወጣት ሴቶች ወደ ከፍተኛው እምቅ አቅማቸዉ ለመድረስ በሚረዳዉ ከትምህርት ሠአት በኋላ ፕሮግራም ላይ በተባባሪነት ስፖንሰር ታደርጋለች። ቀደም ሲልም በ Cabin John፣ Lakelands Park እና Gaithersburg መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች አስተምራለች።

Hanington ለዓመቱ ምርጥ መምህርነት ለፍጻሜ ከተወዳደሩት ከሦስት ተወዳዳሪዎች አንዷ ስትሆን፣ ቀሪዎቹ **Maura Backenstoe**፣ በ Burning Tree አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሙዓለህፃናት አስተማሪ እና **Teak Bassett**በ Clarksburg ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስለ ማህበራዊ ጥናት አስተማሪ ናቸዉ። ለመጨረሻ ዙር የደረሱትን ስያሜ የሰጠው "የማሪያን ግሪንብላት የትምህርት ፈንድ/Marian Greenblatt Education Fund" ነው።

በርካታ ሌሎች የ MCPS ሠራተኞችና የማህበረሰብ አባላትም ላበረከቱት የላቀ አስተዋጽኦ እና ቁርጠኝነት በጀርመንታወን ብላክሮክ የስነጥበብ ማዕከል (BlackRock Center) በተካሄደዉ ለልጆች ሻምፒዮና (Champions for Children) ዝግጅት አስተዋጽኦ እውቅና ተሰጥቷቸዋል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡-

- **Brendan Kelly** በ Einstein ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙዚቃ መሣሪያ አስተማሪ፣ የ Greenblatt Rising Star የዓመቱ መምህር
- **Virginia Pantella**፣ በ Gaithersburg ሚድል ስኩል STEM አስተማሪ፣ የ Greenblatt Rising Star የዓመቱ መምህር

- **Celeste King**, የ South Lake ኤለመንተሪ ት/ቤት ርእሰመምህር፣ የላቀ የትምህርት አስተዳደር እና ሱፐርቪዥን የ Dr. Edward Shirley ሽልማት ተሸላሚ
- **Leslie Atkin** በ Wheaton ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የእንግሊዝኛ ድርሰት ረዳት፣ የዓመቱ የድጋፍ አገልግሎቶች የዓመቱ ሠራተኛ
- **Cynthia Simonson**፣ የ MCCPTA የትምህርት ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚደንት፣ ለልጆች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሻምፒዮና
- **Strathmore**፣ ስለ ልጆች ሽልማት የአጋርነት ሻምፒዮና

ስለ ልጆች የሻምፒዮናዎች ሁነት ተግባራዊ ሊሆን የቻለው በስፖንሰሮች የበጎ አድራጎት ችሮታ ነው። ለዓመቱ የምርጥ መምህር ለመጨረሻዉ ዙር የቀረቡት ሁሉም ተወዳዳሪዎች ከግሪንብላት የትምህርት ፈንድ (Greenblatt Educational Fund) ሁለት ሺህ ዶላር $2,000 ሽልማት አግኝተዋል። የ MCPS የዓመቱ መምህርት እንደመሆኗ መጠን፣ Hanington የአንድ ዓመት የመኪና ሊዝ Fitzgerald ከተባለው ድርጅት ታገኛለች።

**በክረምት የአየር ሁኔታ ምክንያት በ 2018-2019 የትምህርት ቤት ካለንደር ላይ የተደረጉ ለውጦች**
MCPS በዚህ ክረምት አራት ቀኖች ት/ቤቶችን ለመዝጋት አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ አስገድዶታል። በ 2018-2019 የ MCPS ትምህርት ካላንደር የሚያካትተው 182 የትምህርት ቀናት፣ በሜሪላንድ ስቴት ቢያንስ ከሚጠበቀው ገደብ በሁለት ቀናት የበለጠ ነው። በነዚህ መዘጋቶች ምክንያት፣ በስቴት ደረጃ ተፈላጊ የሆኑ የትምህርት ቀኖች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ MCPS ሁለት የማካካሻ ቀኖችን ለመጠቀም ይፈልጋል። የትምህርት ዓመቱ እስከ ጁን 14/2019 ይራዘማል፣ እና ት/ቤቶች ጁን 5 ይከፈታሉ፣ ይህ ቀን ቀደም ሲል ለሠራተኞች ፕሮፌሽናል ቀን እንዲሆን የተያዘ ነበር። ጁን 14 ሁሉም ተማሪዎች በቅድሚያ የሚለቀቁበት ቀን ይሆናል።

[የትም/ቤት ቀን መቁጠርያ]

**ምረቃዎች ሜይ 24 ይጀምራሉ**

የ 2019 የ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የምረቃ ወራት አርብ፣ ሜይ 24 ይጀምርና፣ ሀሙስ፣ ጁን 13 ያልቃል። በ DAR Constitution Hall እና ትብብር የሚካሄደው የምረቃ ስነ-ስርአት [በ DAR ድር-ጣቢያ ]በቀጥታ ይቀርባሉ።

MCPS ወላጆች የሚወዷቸውን የምረቃ ፎቶግራፎች ገቢ እንዲያደርጉ ይጋብዛል። ወላጆች የልጃቸውን/ልጆቻቸውን ከሁሉም የተሻለውን የምረቃ ፎቶ መርጠው በኢሜይል ወደ pio@mcpsmd.org መላክ አለባቸው። ከነዚህ ፎቶግራፎች አብዛኛዎቹ በ MCPS ድረ-ገጽ ይለጠፋሉ። ወላጆችና ተማሪዎች በትዊተር (uበhashtag #mcpsgrad በመጠቀም ፎቶዎችን መላክም ይችላሉ)። ከፎቶዎቹ የተወሰኑትን በማህበራዊ ሚድያ ገፆቻችን መልሰን እንለጥፋቸዋለን።

ፎቶግራፎችን ኢ-ሜይል ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ቀላል እርምጃዎች ተከተሉ:-
- ከሁሉ የላቀውን አግዳሚ ፎቶ ይምረጡ።
- ፎቶዉን በ jpeg file (ከ 4 MB በማይበልጥ) ልካችሁ በ pio@mcpsmd.org ኢ-ሜይል አድርጉ።
- የልጅዎን የመጀመሪያ ስም እና የትምህርት ቤት ስም ያሳውቁ። (የመጨረሻ ስም አናትምም።)

ፎቶውን በመስጠት፣ በ MCPS ድረ-ገፅ እንዲታተም ወላጆች ተስማምተዋል ማለት ነው። ጥያቄ ካለዎት [Department of Public Information and Web Services በስልክ ቁጥር:-240-740-2837 ተገኙ። ወይም በ] pio@mcpsmd.org ኢ-ሜይል አድርጉልን።

[Graduation dates and locations]

**ሜይ 8 "የሳይንስ ምሽት/Science Night" በ Wootton ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ይካሄዳል**

ስለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዋና የሳይንስ ኮርስ አማራጮች የላቀ Advanced Placement (AP) እና International Baccalaureate (IB) ኮርሶችን ጨምሮ ሜይ 8 ከ 6:30 p.m. እስከ 8:30 p.m. በ ውተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Wotton High School ስለሚካሄድ ወላጆች እና ተማሪዎች ይበልጥ ግንዛቤ ለማግኘት እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል። ሁነቱ በ MCPS እና MCCPTA አማካይነት ስፖንሰር ይደረጋል። ሁነቱ በሚካሄድበት ወቅት ወላጆች ግንዛቤ/እዉቀት የሚያገኙት ስለ፦

- ከ 9ኛ እስከ 12ኛ ክፍሎች Advanced Placement (AP) እና International Baccalaureate (IB) ኮርሶችን ጨምሮ እያንዳንዱን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሳይንስ ኮርስ አማራጮች
- ለኮሌጅ እና የሙያ ሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞችን የሚያካትት፣ አዲስ እና የሚያጓጓ የሳይንስ ኮርስ ፈለግ።
- ለሜሪላንድ የተቀናጀ የሳይንስ ምዘና/Maryland integrated Science Assessment (MISA) በተለይ የሁለተኛ ደረጃ መመረቂያ መስፈርቶች
- በሜሪላንድ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደረጃ የጠበቀ የመጪው ትውልድ ሳይንስ/The Next Generation Science Standards (NGSS) in Maryland and MCPS

የልጆች እንክብካቤ እና የትርጉም አገልግሎት ይኖራል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት RSVP ይህንን ይጫኑ።

**MCPS ስለ ኤለመንተሪ ት/ቤት ሒሳብ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ-ጥበብ ከሪኩለም ለወላጆች የመረጃ ልውውጥ ምሽት ይካሄዳል**

MCPS ለኤለመንተሪ እና ለሚድል ስኩል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ (ELA) እና ሒሳብ ከፍተኛ ደረጃ ጥራት ያለው ለሁሉም ተማሪዎች ማስተማር እና መማርን ለመደገፍ ለሦስት ዓመት የሚዘልቅ አዲስ ከሪኩለም መተግበር ይጀምራል። ይምጡና ከ MCPS ሠራተኞች እና ከአዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት አፍላቂዎች በት/ቤቶቻችን ምን እንደሚተገበሩ የበለጠ ይማሩ። Math እና ELA የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሪኩለም የሚቀርብ ሲሆን ተሳታፊዎች ጥያቄዎችን የማቅረብ እድል ይኖራቸዋል።

የመረጃ ልውውጥ ምሽቶቹ የሚካሄዱት በሚከተሉት ቀኖች ነው፦

ማክሰኞ፣ ሜይ 21/2019
ሠዓት፦ 7:00-9:00 p.m.
ቦታ፦ ፔይንት ብራንች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Paint Branch High School

ረቡእ፣ 22/2019
ሠዓት፦ 7:00-9:00 p.m.
ቦታ፦ ጌትስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/Gaithersburg High School

ማክሰኞ ሜይ 23/2019
ሠዓት፦ 7:00-9:00 p.m
ቦታ፦ ሮክ ረሬስ ትምህርት ቤት/Rock Terrace School

የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ለመመዝገብ/RSVP፣ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

**ናትናኤል ትንቢት/Nathaniel Tinbite በትምህርት ቦርድ ቀጣዩ የተማሪ አባል በመሆን ተመርጧል**

ናትናኤል ትንቢት/Nathaniel Tinbite፣ በ ጆን ኤፍ ኬኔዲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (John F. Kennedy High School) ጁንየር ተማሪ ለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት የትምህርት ቦርድ የተማሪ አባል (SMOB) በመሆን ተመርጧል። የአቶ ትንቢት የአገልግሎት ጊዜ የሚጀምረው ጁላይ 1/2019 ነው። የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሙሉ ተማሪ የቦርድ አባል (SMOB) ለመምረጥ የሚችሉ ሲሆን 85.19 ፐርሰንት ድምፅ ሰጥተዋል።

አቶ ትንቢት/Mr. Tinbite 74 ፐርሰንት ድምፅ አግኝቷል፣ የእርሱ ተፎካካሪ የክላርክስበርግ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ጁንየር የሆነው Zoe Tishaev 26 ፐርሰንት አግኝቷል።

አቶ ትንቢት/Mr. Tinbite በአሁን ወቅት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ሪጅናል (MCR) የተማሪዎች አመራር ህብረት (SGA) ፕሬዚደንት በመሆን እያገለገለ ሲሆን "MoCo for Change" መሥራችም ነው። በተጨማሪ በ MCR ምክትል ፕሬዚደንትነት እና ለቀድሞው SMOB, Matthew Post ቺፍ ኦቭ ስታፍ በመሆን አገልግሏል።

ተማሪ የቦርድ አባል (SMOB) የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ድምፅ የሚሰጥ/የምትሰጥ አባል ነው/ናት። ተማሪ የቦርድ አባል (SMOB) የጋራ ድርድር፣ የካፒታል፣ እና የሥራ ማስኬጃ በጀት እና ት/ቤቶች ሲዘጉ፣ እና ዳግመኛ ሲከፈቱ እና በት/ቤቶች ወሰን-ድንበር ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ድምፅ ይሰጣል/ትሰጣለች። SMOB በአሉታዊ የሰው ኃይል እርምጃዎች/ትግባሬዎች ላይ ድምፅ አይሰጥም። SMOB ክፍያ የለውም፣ $5,000 የኮሌጅ ስኮላርሽፕ፣ የተማሪ አገልግሎት ሠዓቶች፣ እና አንድ የላቀ-ደረጃ የማህበራዊ ጥናት ክሬዲት ይሰጣል።

አቶ ትንቢት/Mr. Tinbite የሚተካው ጁን ላይ የምትመረቀውን የወቅቱን SMOB፣ የሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲንየር የሆነችውን Ananya Tadikonda ን ነው።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት ተማሪ የቦርድ አባል ድረገጽ ይጎብኙ፡-

**የ 2019 የጌትስበርግ መጽሐፍ ትዕይንት እንዳያመልጥዎት**

የ 2019 የጌትስበርግ የመጻህፍት አውደርዕይ ቅዳሜ፣ ሜይ 18፣ የጌትስበርግ ሲቲ አዳራሽ በሚገኝበት ግቢ Gaithersburg City Hall, 31 S. Summit Avenue in Gaithersburg ይካሄዳል።

አውደርዕይ ላይ እውቅ ደራሲያን እና በሁሉም የእድሜ ክልል ላይ ለሚገኙ ህፃናት የሚሆኑ ዝግጅቶች ይቀርባሉ። በርካታ የ MCPS ማህበረሰብ አባላት በፌስቲቫሉ ላይ ምንባቦች፣ እና ፕሮግራሞች፣ አውደጥናቶች፣ እና በልጆች መንደር ስለምንባብ እና ስነጽሑፍ ፍላጎት የሚያነቃቁ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይቀርባሉ።

ከ 100 በላይ ደራሲዎች እንደሚገኙ በጊዜ ሠሌዳው ተገልጿል። ስለ ልጆች እና ወጣት ጎልማሳ ደራሲያን መካከል Zeno Alexander፣ Fred Bowen፣ Amy Ewing፣ Jessica Day George፣ እና Monica Hesse ይሳተፋሉ። ስለ ስነጽሑፍ ከሚካሄዱት አውደጥናቶች ጥቂቶቹ ጉጉት/አጠራጣሪ ነገር እንዴት እንደሚገነባ፣ የፈጠራ ጽሁፍ በስፓንሽ፣ እና ስለ ጋዜጣ/መጽሔት/የእለት ማስታወሻ አፃፃፍን ይሸፍናል።

ስለ ሁነቱ ዝግጅት የበለጠ መረጃ ለማግኘት www.gaithersburgbookfestival.org ይጎብኙ።

**ለ 2019 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙያ ሥራ ዝግጁነት ሠመር ካምፕ ምዝገባ ክፍት ነው**

በ MCPS የ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በዚህ ዓመት በሚካሄደው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሥራ ሙያ ዝግጁነት የሠመር ካምፖች እንዲሣተፉ ተጋብዘዋል። ተማሪዎች በክህሎት እና በሙያዊ ዕውቀት ስለሚሠሩ ሥራዎች ልምድ የመዳሰስ እና ከዝንባሌያቸው እና ግቦቻቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ በ MCPS የሚሠጡ አካዳሚዊያ የሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞችን የመዳሰስ እድል ይኖራቸዋል። ካምፑ ከንድፍ ሥራ እና ከአቶሞቲቭ (architecture and automotive ) እስከ ሳይበር ሰኩሪቲ፣ spa አገልግሎቶችን፣ የግንባታ መሠረተ ሥራዎች እና ኮምፒውተሮችን መሥራት እና መጠገን ጨምሮ ስድስት ፕሮግራሞችን ይሰጣል። ካምፖቹ የሚካሄዱት ከ 8:15 a.m.–1:00 p.m. በቶማስ ኤድስን ሁለተኛ ደረጃ የቴክኖሎጂ ት/ቤት (Thomas Edison High School of Technology) ከጁላይ 15/2019 እስከ ኦገስት 2/2019 ይሆናል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት እና ለመመዝገብ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

የሠመር ዝግጁነት ካምፖች/Summer Readiness Camps

**የ LGBTQIA ፎረም ሜይ 18 ይካሄዳል**

MCPS፣ ከ MCCPTA እና ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር በመተባበር ጠንካራ እና የብዝሃነት LGBTQIA መገንባትን ለማገዝ ሜይ 18 ፎረም ያካሄዳል። ፎረሙ የሚካሄደው በ Thomas S. Wootton ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ 9–12 p.m. ነው። በድረ-ገጽ ለመመዝገብ - RSVP ይህንን አውታረ-መረብ ይጎብኙ https://mcpsweb.wufoo.com/forms/lgbtqia-rsvp-form/።